# የመንገድ ደህንነት እና መድን ፈንድ አገልግሎት

# Road Safety and Insurance Fund Service

## የተሽከርካሪ አደጋ የሶስተኛ ወገን መድን የመድን ውልና የካሳ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር /-------/

## መግቢያ

የሶስተኛ ወገን መድን ሽፋን በተገባላቸው ወይም መድን ሽፋን ሳይኖራቸው በመንገድ ላይ ሊነዱ ወይም ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ተሽከርካሪዎች በሶስተኛ ወገን ላይ ለሚያደርሱት ጉዳት ካሳ የሚከፈልበት ሁኔታ፣ተደጋጋሚ አደጋ የሚያደርሱ መድን ገቢዎችና አሽከርካሪዎች ላይ ስለሚወሰድ እርምጃ፣ ከአንድ አመት ላነሰ ጊዜ የሚሰጥ የመድን ፖሊሲ የውል ዘመኑን መሰረት ያደረገ የመድን ምስክር ወረቀትን በተመለከተ እና ሌሎች የአሰራር ዝርዝር ሊቀመጥላቸው የሚገቡ ጉዳዮችን በተመለከተ ዝርዝር ድንጋጌዎች በማስቀመጥ የአዋጁን አፈፃፀም የተሻለ ማድረግ እና በአገር አቀፍ ደረጃ አንድ ወጥ የሆነ አሰራር መርዝርጋት በማስፈለጉ የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር በተሽከርካሪ አደጋ የሶስተኛ ወገን መድን አዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## የመመሪያው ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ የመድን ውልና ካሳ አፈጻጸም አስተዳደርን ዲጂታላይዝ በማድረግ በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ አሰራር እንዲኖር ለማስቻል፤የተሽከርካሪ አደጋ የመድን ውል የሚከፈለውን የአረቦን ተመን እና የካሳ መጠን ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣውን ደንብ ተፈጻሚነት ለማረጋገጥ እና የተሽከርካሪ አደጋ ሶስተኛ ወገን ተጎጂዎች ተገቢውን ካሳ ከመድን ሰጪ ኩባንያዎች ወይም ከአገልግሎቱ ስለማግኘታቸው ለማረጋገጥ ነው፡፡

## የመመሪያው አስፈላጊነት

በነባሩ የተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን ውል እና የካሳ አፈፃፀም መመሪያ አፈፃፀም የታዩ ችግሮችና ያልተካተቱ ጉዳዮች በመኖራቸው እነዚህን እና ሌሎች ተያያዥ ድንጋጌዎችን ያካተተ ህግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የመረጃ አያያዝ ስርዓቱ በመዘመኑ እና በባህር መዝገብ ላይ በመመዝገብ ሳይሆን በኦንላይን ሲስተም በመተካቱ በሚሻሻለው መመሪያ ውስጥ ይህንን ማካተት በማስፈለጉ፣

በደንብ ቁጥር 300/2006 ተቋቁሞ የነበረው የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ በአዲስ መልክ በደንብ ቁጥር 493/2014 የመንገድ ደህንነት እና መድን ፈንድ አገልግሎት ሆኖ በመቋቋሙ ይህንን በሚሻሻለው መመሪያ ውስጥ ማካተት በማስፈለጉ መመሪያው ተሻሽሏል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ «የተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን ውል እና የካሳ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር……» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጎሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፦

1. በአዋጅ ቁጥር 799/2005 እና በደንብ ቁጥር 493/2014 የተተረጎሙት ቃላት ለዚህም መመሪያ ተፈፃሚ ይሆናሉ፤
2. **«አዋጅ»** ማለት የተሽከርካሪ አደጋ የሶስተኛ ወገን መድን አዋጅ ቁጥር 799/2005 ነው፤
3. **"ደንብ"** ማለት የመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 493/2014 ነው፤
4. **«አገልግሎት»** ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 493/2014 የተቋቋመው የመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት ነው፤
5. **«ዲጂታል የሶስተኛ ወገን መድን»** ማለት የዲጂታል ቴክኖሎጂ ስርዓትን በመጠቀም የሶስተኛ ወገን መድን ለተጠቃሚዎች ማቅረብ እና ማስተዳደር ነው፡፡
6. **«ዲጂታል የመድን ምስክር ወረቀት»** ማለት የተሽከርካሪ ባለንብረት ለተሽከርካሪ አደጋ የ3ኛ ወገን መድን የገባ መሆኑን የሚያረጋግጥ እና ከዲጂታል ሲስተም ታትሞ በተሽከርካሪ የፊት መስታወት የሚቀመጥ ወይም የፊት መስታወት ለሌላቸው ተሽከርካሪዎች በአሽከርካሪዎች እጅ የሚቀመጥ ሰነድ ነው ::
7. **«የአደጋ መመዝገቢያ ስርዓት»** ማለት አንድ መድን በተገባለት ተሽከርካሪ የመድን ሽፋን ውሉ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ በሲስተም የተመዘገበ የጉዳት ብዛት የሚያሳይ ነው፤

8. **«መድን ያልተገባለት ተሽከርካሪ »**ማለት በአዋጁ መሠረት የጸና የ3ኛ ወገን መድን ሽፋን የሌለው ተሽከርካሪ ወይም የኢንሹራንስ ሽፋን ቢኖረውም የመድን ሽፋኑን የሰጠው የመድን ኩባንያ በመክሰሩ ምክንያት ካሳ ለመክፈል አቅም ያጣ ነው፤

9. **«ያልታወቀ ተሽከርካሪ»** ማለት አደጋ ያደረሰው ተሽከርካሪ፣ አሽከርካሪው እና ባለንብረቱ ያልታወቀ ተሽከርካሪ ነው፤

10. **«የህክምና ወጪ»** ማለት በተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ሰው በሕክምና ተቋም ውስጥ ተኝቶ ወይም በተመላላሽነት ሲታከም የወጣ የህክምና ወጪ ሲሆን የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ወጪን አያካትትም፤

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአገልግሎቱ፣ በመድን ሰጭ፣ በመድን ገቢዎች እንዲሁም በተሽከርካሪ አደጋ ጉዳት በደረሰባቸው ሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

# ክፍል ሁለት

## ዲጂታል የሶስተኛ ወገን መድን አስተዳደር አሰራር፣

## 4. የዲጂታል የሶስተኛ ወገን መድን አስተዳደር አሰራር

1. አገልግሎቱ የተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን ሽፋን እንዲኖራቸው በአስገዳጅነት ለተደነገገባቸው ተሽከርካሪዎች የሚያገለግል ዲጂታል የሶስተኛ ወገን መድን ስርዓትን ይዘረጋል።
2. አገልግሎቱ የመድን ሰጪዎች ለደበኞቻቸው የሰጡትን ዲጂታል የሶስተኛ ወገን መድን ሽፋን ቁጥጥር እና ክትትል የማድረግ ሃላፊነት አለበት።
3. መድን ሰጪዎች የሚሰጡት የዲጂታል የመድን ምስክር ወረቀት በሙሉ ተከታታይ የሆነ ቁጥር ይኖራቸዋል።
4. እያንዳንዱ የዲጂታል የመድን ምስክር ወረቀት ከላይ የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክ ሚንስቴር እና የአገልግሎቱ አርማ መያዝ አለበት።

5. እያንዳንዱ የዲጂታል የመድን ምስክር ወረቀት በአዋጁ አንቀጽ 9 እና ሌሎች ድንጋጌዎች እና መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የዲጂታል የመድን ምስክር ወረቀቱ የሚከተሉትን መረጃዎች ይይዛል፡፡

ሀ.የመድን ውል ቁጥር

ለ. የመድን ምስክር ወረቀት ቁጥር

ሐ.የመድን ገቢው ስምና አድራሻ

መ. የተሽከርካሪው የሰሌዳ ፤የሞተር እና የሻንሲ ቁጥሮች

ሠ. የመድን የውል ዘመን

ረ. የተሽከርካሪው አገልግሎት፤ የመጫን አቅም በሰው እና በኩንታል

ሰ. የመድን ሰጭው ስምና ቅርጫፍ

ሸ. የመድን ሰጭው ማሕተም

## 5. ዲጂታል የሶስተኛ ወገን የመድን ምስክር ወረቀት አሰጣጥ

ማንኛውም መድን ሰጪ ዲጂታል የመድን ምስክር ወረቀት ሲሰጥ የሚከተሉትን ዝርዝር የስራ መመሪያዎች ማክበር አለበት፤

1. ማንኛውም መድን ሰጭ የሚሰጠው ዲጂታል የመድን ምስክር ወረቀት በዚህ መመሪያ መሰረት አገልግሎቱ በዘረጋው የዲጅታል ሶስተኛ ወገን መድን አስተዳደር ስርዓት ብቻ መሆን አለበት፡፡
2. ማንኛውም መድን ሰጭ በዲጂታል ቴክኖሎጂ የሦስተኛ ወገን መድን ስርዓት መሠረት ለሶስተኛ ወገን መድን ገቢው ውል የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡
3. ማንኛውም መድን ሰጭ በዲጂታል የሶስተኛ ወገን መድን ምስክር ወረቀት ላይ ሊካተቱ የሚገባቸው መረጃዎችን በሙሉ በግልጽ እና በአግባቡ መሙላት አለበት፡፡
4. አንድ የዲጂታል የሶስተኛ ወገን መድን ምስክር ወረቀት የሚዘጋጀው እና የሚያገለግለው ለአንድ ተሽከርካሪ ብቻ ነው፡፡
5. ማንኛውም መድን ሰጭ ለእያንዳንዱ ተሳቢ ወይም ግማሽ ተሳቢ አንድ የራሱ የሆነ የዲጂታል የሶስተኛ ወገን መድን ምስክር ወረቀት መስጠት ያለበት ሲሆን የዲጂታል መድን ምስክር ወረቀት የሚሰጠውም የመድን ሽፋን ውል በሰጠው መድን ሰጭ ኩባንያ ብቻ ነው፡፡
6. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም መድን ሰጭ የሚሰጠው የዲጂታል የመድን ምስክር ወረቀት የሚጸናበት ጊዜ ከአንድ አመት ያላነሰ መሆን አለበት፡፡

## 6. የመድን ውል ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ

1. የመድን ውል ፀንቶ የሚቆየው ከአንድ አመት ላላነሰ ጊዜ የሚጸና መሆን አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሚከተሉት ምክንያቶች ብቻ ከአንድ አመት ላነሰ አጭር ጊዜ ሊሰጥ ይችላል፡፡

   ሀ/ አንድ አስመጪ ያስመጣቸው ተሽከርካሪዎች እስከሚሸጥ ድረስ ላለው ጊዜ

   ለ/ ከወደብ ወደ ሀገር የሚገባ ተሽከርካሪን በተመለከተ፣

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ቢኖርም ከአስር ቀን በታች ለሆነ ጊዜ የ3ኛ ወገን የመድን ሽፋን መስጠት አይቻልም፡፡
4. ከአንድ አመት በታች ለአጭር ጊዜ ለሚሰጥ የመድን ሽፋን የአረቦን ተመን የሚሰላው በተከታዩ ሰንጠረዥ መሠረት ነው፡-

| የውል ዘመን | ከአመቱ አረቦን ላይ የሚከፈል |
|---|---|
| ከ10 ቀን እስከ 1ወር | 30% |
| ከ2 ወር ለማይበልጥ | 50% |
| ከ3 ወሮች ለማይበልጥ | 70% |
| ከ4 ወሮች ለማይበልጥ | 80% |
| ከ5 ወሮች ለማይበልጥ | 90% |
| ከ6 ወሮች ከበለጠ | የአንድ አመት አረቦን |

5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ድንጋጌ ቢኖርም ለአጭር ጊዜ ለሚሰጥ የመድን ውል ሽፋን የሚከፈለው አነስተኛው የአረቦን መጠን ከ809 (ስምንት መቶ ዘጠኝ) ብር ማነስ አይችልም፡፡

## 7. የመድን ውል ስለመሰረዝ

1. የመድን ውል የሚሰረዘው ተሽከርካሪው የወደመ ወይም ከጥቅም ውጪ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ለተሰረዘው የመድን ውል ቀሪ ጊዜ የሚሰላው የአረቦን እና የፈንድ ተመን ድርሻ ተመላሽ አይሆንም፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገው እንደተተበቀ ሆኖ የመድን ሽፋን የተገባለት ተሽከርካሪ ለሦስተኛ ሰው በሽያጭ በስጦታ ወይም በሌላ ማንኛውም ሁኔታ ቢተላለፍ ሽፋኑ አይቋረጥም፡፡

4. የመድን ሽፋን የተገባለት ተሽከርካሪዎች አገልግሎታቸውን ሲቀይሩ የአረቦን መጠን የሚጨምር ከሆነ የዲጂታል ስርዓቱ አዲሱን የአረቦን ክፍያ ያሰላል፡፡ አዲሱ የአረቦን መጠን ከቀዳሚው ክፍያ የበለጠ ከሆነ ባለንብረቱ ልዩነቱን ለመድን ሰጪ ኩባንያው ከፍሎ ሽፋኑ የአገልግሎቱ ጊዜ እስከቢያበቃ ድረስ ይቀጥላል፡፡

## 8. የጠፋ ወይም የተበላሸ የዲጂታል ህትመት የመድን ምስክር ወረቀት

1. ማንኛውም መድን ገቢ ወይም አሽከርካሪ ዲጂታል የመድን ምስክር ወረቀት አትሞ መያዝ አለበት፡፡
2. ማንኛውም መድን ገቢ ወይም አሽከርካሪ አትሞ የያዘው የዲጂታል የመድን ምስክር ወረቀት የጠፋ ወይም የተበላሸ እንደሆነ እንደገና ከዲጂታል ሲስተም አትሞ መያዝ አለበት፡፡

## 9. የፈንድ ገቢ አሰባሰብ

1. የሶስተኛ ወገን መድን ፈንድ ገቢ በተዘረጋው የዲጅታል የአሰራር ስርዓት መሰረት ለዚህ ተብሎ በተከፈተ ልዩ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ተቀማጭ ይሆናል፡፡
2. የሶስተኛ ወገን ፈንድ ገቢ የሂሳብ ዘመኑ የሚሆነው የሂሳብ ዘመኑ ከሀምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ነው፡፡

# ክፍል ሶስት

# ተደጋጋሚ አደጋ ስለሚያደርሱ መድን ገቢዎች

## 10. አደጋ ስለመመዝገብ

ማንኛውም መድን ሰጭ መድን ገቢዎች የሚያደርሱትን አደጋ እና ጉዳት መጠን በተዘረጋው የዲጂታል የሶስተኛ ወገን የአስተዳደር ስርዓት መመዝገብ አለበት፡፡

## 11. ተደጋጋሚ የትራፊክ አደጋ የሚያደርሱ መድን ገቢዎች ላይ ስለሚወሰደው እርምጃ

1. ማንኛውም መድን ሰጭ ለመድን ገቢ የዲጂታል ሶስተኛ ወገን መድን ሽፋን ውል እድሳት ከማድረጉ በፊት መድን የተገባለት ተሽከርካሪ በአለፈው ዓመት የመድን ሽፋን ውል ያደረሰው አደጋ እና የጉዳት መጠን ማጣራት አለበት፡፡
2. ማንኛውም የዲጂታል የሶስተኛ ወገን መድን ሽፋን የተገባለት ተሽከርካሪ በአንድ የውል ዓመት ውስጥ ያደረሰው አደጋ እና የጉዳት መጠን ተሰልቶ በቀጣይ ዓመት የአረቦን ተመን ላይ ጭማሪ ያደርግበታል፡፡
3. የአረቦን ክፍያ የሚተመነው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተገኘው መረጃ መሠረት ቀድሞ በስሙ በተመዘገቡ የአደጋ ብዛት እና መጠን መሠረት ሲሆን የጉዳት ዓይነቶች እና የአረቦን መጠኑ በምን ያህል እንደሚያድግ የሚገልጽ አባሪ ሰነድ መያያዝ አለበት፡፡
4. ማንኛውም መድን ሰጭ የመድን ውል በሚያድስበት ጊዜ መድን የተገባለት ተሽከርካሪ በአንድ አመት ውስጥ የተመዘገበበትን አደጋ እና የጉዳት መጠን መሠረት ያደረገ አረቦን በማስላት ይሰበስባል፡፡
5. የአረቦን ጭማሪ አሰላል የአደጋ አይነት እና ጉዳት መጠንን ከግምት ባስገባ ሁኔታ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 መሠረት ይሰላል፡፡

## 12. ስለ ኃላፊነት

1. የዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 ድንጋጌ ቢኖርም መድን ገቢው ለደረሰው አደጋ ኃላፊ ያልሆነ እንደሆነ የአረቦን ጭማሪ አይደረግበትም፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም በአደጋው ተካፋይ የሆነው ተሽከርካሪ አንድ ብቻ የሆነ እንደሆነ ለአደጋው ኃላፊነት አለበት፡፡
3. በአደጋ ተካፋይ የሆኑት ተሽከርካሪዎች ቁጥር ከአንድ በላይ የሆኑ እንደሆነ ኃላፊነት ያለበት ተለይቶ የሚታወቀው በፖሊስ ሪፖርት ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ ነው፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተጠቀሰው አይነት አደጋ ባጋጠመ ጊዜ የተሽከርካሪዎቹ ኃላፊነት መጠን የሚወሰነው ለአደጋው መድረስ ባላቸው አስተዋፅኦ ወይም ስህተት መሰረት ነው፡፡

## 13. የአረቦን ተመን አሰላል

ተደጋጋሚ የትራፊክ አደጋ የሚያደርሱ መድን ገቢዎች የሚያደርሱትን አደጋ እና የጉዳት መጠን ያገናዘበ የአርቦን ተመን ለመወሰን ስሌቱ የሚከተለውን ሰንጠረዥ መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡

| | የአደጋው አይነት | የመጀመሪያ አደጋ | ሁለተኛ አደጋ | ሦስተኛ አደጋ | አራተኛ አደጋ | አምስተኛ አደጋ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የአካል ጉዳት | | | | | |
| 1.1 | ቀላል የአካል ጉዳት | 10% | 20% | 50% | 80% | 100% |
| 1.2 | ከባድ የአካል ጉዳት | 20% | 30% | 50% | 80% | 100% |
| 1.3 | የሞት አደጋ | 50% | 75% | 85% | 100% | 100% |
| 2 | የንብረት ጉዳት | | | | | |
| 2.1 | ከብር50000 በታች | 10% | 20% | 30% | 50% | 100% |
| 2.2 | ከ50001እስከ100000 | 20% | 30% | 75% | 100% | 120% |
| 2.3 | ከ100001እስከ500000 | 50% | 75% | 100% | 120% | 130% |
| 2.4 | ከ500001እስከ1000000 | 60% | 80% | 110% | 130% | 140% |
| 2.5 | ከ1000001 በላይ | 70% | 90% | 120% | 135% | 150% |

## 14. የአረቦን ጭማሪ የሚቆይበት ጊዜ

1. በማንኛውም መድን ገቢ ላይ ተደጋጋሚ አደጋ በማድረስ ምክንያት የአረቦን ጭማሪ የተደረገበት እንደሆነ የአርቦን ጭማሪው ለቀጣዩቹ 3 ዓመታት ጸንቶ ይቆያል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ መድን ገቢው ለቀጣዮቹ 3 ዓመታት አደጋ ያላደረሰ እንደሆነ የአረቦን ተመኑ ቀድሞ ወደነበረበት መጠን ዝቅ እንዲል ይደረጋል፡፡

## 15. መድን ሰጭ ኩባንያ ስለመቀየር

ማንኛውም መድን ገቢ የመድን ግንኙነቱን ከአንድ መድን ሰጪ ኩባንያ ወደ ሌላ መድን ሰጪ ኩባንያ በሚቀይርበት ጊዜ ሌላኛው መድን ሰጪ ኩባንያ ባለፉት 3 ዓመታት መድን በተገባለት ተሽከርካሪ ስም የተመዘገበ አደጋ ስለመኖር አለመኖሩ ከዲጂታል ስርዓቱ በማጣራት በዚህ መመሪያ መሰረት ሽፋን መስጠት አለበት፡፡

# ክፍል አራት

# በአገልግሎቱ እና በመድን ሰጪ ኩባንያዎች የሚፈጸም የካሳ አከፋፈል ዝርዝር ሁኔታ

## ንዑስ ክፍል አንድ

## በአገልግሎቱ የሚፈጸም የካሳ አከፋፈል ዝርዝር ሁኔታ

### 16. አደጋን የማሳወቅ ተግባር

1. መድን በሌለው ተሽከርካሪ እና ባልታወቀ ተሽከርካሪ የደረሰ ማንኛውም አደጋ አደጋው ከደረሰ ጀምሮ ባሉት 10 (አስር) ቀናት ውስጥ ለአገልግሎቱ መግለጽ አለበት፡፡
2. መድን በሌለው ተሽከርካሪ እና ባልታወቀ ተሽከርካሪ የደረሰ አደጋን ማሳወቅ የሚችሉት፡-

   ሀ. ተጎጂው ወይም ከተጎጂው ወይም አግባብ ካለው አካል የተሰጠ ሕጋዊ ውክልና ያለው ሰው፡፡

   ለ. የትራፊክ ፖሊስ ወይም ሌላ መንግስታዊ አካል፣

   ሐ. የአስቸኳይ ሕክምና አገልግሎት የሰጠ ተቋም፣

   መ. አደጋውን የሚያውቅ በአደጋው ቦታ የነበረ ማንኛውም ሰው፤

3. ማንኛውም ሰው መድን በሌለው ተሽከርካሪ እና ባልታወቀ ተሽከርካሪ የደረሰ አደጋን ወይም የካሳ ጥያቄን በስልክ፣ በፋክስ፣ በኢሜል፣ በደብዳቤ ፤ በአገልግሎቱ ዌብ ሳይት ወይም በመንገድ ትራፊክ አደጋ መረጃ አስተዳደር ስርዓት መሰረት ለፖሊስ  ወይም ለአገልግሎቱ ማሳወቅ ይችላል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ከተጠቀሰው በተጨማሪ አገልግሎቱ ለዚሁ ባዘጋጀው መድን የሌላቸው ተሽከርካሪዎች አደጋ ማሳወቂያ ቅጽ፣ ባልታወቁ ተሽከርካሪዎች አደጋ ማሳወቂያ ቅጽ እና የትራፊክ ፖሊስ የሚሞላው የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት መጠየቂያ ቅጽ አማካኝነት አደጋውን ማሳወቅ ይችላል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 በተጠቀሱት መንገዶች አገልግሎቱ እንዲያውቃቸው የተደረጉ አደጋዎች ወይም የካሳ ጥያቄዎች በአገልግሎቱ ወይም በክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች በትራንስፖርት ቢሮ የተደራጁ የድህረ ትራፊክ አደጋ የስራ ክፍሎች ወዲያው ለሚመለከተው ለአገልግሎቱ የድህረ ትራፊክ አደጋ አገልግሎት እና መድን አስተዳደር መሪ ሥራ አስፈፃሚ የስራ ክፍል መድረስ አለበት፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 በተመለከቱት መንገዶች አደጋው ወይም የካሳ ጥያቄው በአገልግሎቱ እንደታወቁ ጉዳዩ የተመራለት የድህረ ትራፊክ አደጋ መድን አገልግሎት ዘርፍ የሚመለከተው ሰው ወይም አመልካቹ እንደአግባብነቱ መድን የሌላቸው ተሽከርካሪዎች አደጋ ወይም ያልታወቁ ተሽከርካሪዎች አደጋ ማሳወቂያ ቅጽ ወይም በዲጂታል ስርዓት አመዘጋገብ መሰረት ወዲያዉኑ እንዲሞላ ማድረግ አለበት፡፡
7. አደጋውን ወይም የካሳ ጥያቄውን ያሳወቀው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት ቅጹን ከሞላ ወይም በዲጂታል አመዘጋገብ ስርዓት ከተመዘገበ በኋላ ይህንኑ የተሽከርካሪ አደጋ ለትራፊክ ፖሊስ፣ ለፖሊስ ወይም ለመንግስታዊ አካል በወቅቱ ማሳወቁን የሚያስረዳ ማረጋገጫ ማቅረብ ወይም በመንገድ ትራፊክ አደጋ መረጃ አስተዳደር ስርዓት መሰረት መረጋገጥ አለበት ፡፡

## 17. አደጋውን ወይም የካሳ ጥያቄውን የመመዝገብ ሥርዓት

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 በተጠቀሱት መንገዶች መድን በሌለው ተሽከርካሪ ወይም ባልታወቀ ተሽከርካሪ የደረሰ አደጋ እንዲያውቅ የተደረገ የድህረ ትራፊክ አደጋ መድን አገልግሎት የስራ ዘርፍ አስፈላጊ መረጃዎችን በመሰብሰብ በዲጂታል ስርዓት አመዘጋገብ መሰረት እንዲመዘገብ በማድረግ ክትትል ያደርጋል፡፡
2. በአዋጅ መሠረት ካሳ የመጠየቅ መብት ያለው ሰው ወይም ሕጋዊ ተወካዩ ወይም ሌላ አካል ያሳወቀውን አደጋ ለአገልግሎቱ ባዘጋጀው የዲጂታል የአመዘጋገብ ስርዓት በመመዝገብ ማህደር ይከፍታል፡፡
3. በአመዘጋገብ ስርዓት ላይ የተጠቀሰው የማኅደር ቁጥር ከካሳ ጠያቂው ጋር እና ከሌሎች ወገኖች ጋር በሚደረግ የጽሑፍ ግንኙነት መግለጫ ይሆናል፡፡
4. መድን በሌላቸው እና ባልታወቁ ተሽከርካሪዎች የደረሱ አደጋዎች የሚቀርቡ የካሳ ጥያቄዎች የተለያዩ የአመዘጋገብ ስርዓት ይኖራቸዋል፡፡

## 18. መድን የሌለው ተሽከርካሪ የተመለከተ የካሳ ጥያቄ የአመዘጋገብ ስርዓት ይዘት

መድን በሌላቸው ተሽከርካሪዎች የደረሱ አደጋዎች የሚቀርቡ የካሳ ጥያቄዎች የሚመዘገቡበት የአመዘጋገብ ስርዓት የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡-

1. አደጋው ወይም የካሳ ጥያቄው በአገልግሎቱ የአመዘጋገብ ስርዓት የተመዘገበበት ቀን
2. የካሳ ማህደር ቁጥር
3. መየተ/ክልልለ/000/ዓ.ም በሚል በአጭር የተፃፉ በሚመለከተው መንገድ የሚተረጎሙ፡-

   ሀ. መየተ፡-መድን የሌላቸው ተሽከርካሪዎች

   ለ. ክልል፡-አደጋው የደረሰበት ክልል

   ሐ. 000፡-የካሳ መዝገብ ላይ የተመዘገበበት ቁጥር

   መ. ዓ.ም፡-ዓመተ ምህረት/ዘመን

4. የተጎጂው ስም፤የአደጋው ቀን እና የአደጋው ቦታ
5. አደጋውን ያደረሰው አሽከርካሪ ስምና አድራሻ፤የተሽከርካሪው ሰሌዳ ቁጥር እና የተሽከርካሪው ባለቤት ስምና አድራሻ

6. አደጋውን የመረመረው ትራፊክ ፖሊስ፣ ፖሊስ ወይም መንግስታዊ አካል ስምና አድራሻ
7. የካሳ ክፍያ መጠን
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 መሠረት የሚገለጸው የካሳ መጠን የሚከተሉትን ዝርዝሮች መያዝ አለበት

   ሀ. የተያዘ አጠቃላይ መጠባበቂያ

   ለ. የሕክምና አገልግሎት (የተከፈለ፣ቀሪ)

   ሐ. አካል ጉዳት (የተከፈለ፣ቀሪ)

   መ. ሞት (የተከፈለ፣ቀሪ)

   ሠ. ሌሎች ክፍያዎች

   ረ. አጠቃላይ ክፍያ

9. በዚሁ አንቀጽ ንዕስ አንቀጽ 1-8 ከተጠቀሰው የካሳ ጥያቄ የአመዘጋገብ ስርዓት በተጨማሪ አገልግሎቱ ለዚህ ብሎ በአዘጋጀው የዲጂታል ስርዓት መሰረት ይመዘግባል፡፡

## 19. ያልታወቀ ተሽከርካሪን የተመለከተ የካሳ ጥያቄ የአመዘጋገብ ስርዓት ይዘት

ባልታወቀ ተሽከርካሪ የደረሱ አደጋዎች የሚቀርቡ የካሳ ጥያቄዎች የአመዘጋገብ ስርዓት የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡-

1. አደጋው ወይም የካሳ ጥያቄው በአገልግሎቱ የአመዘጋገብ ስርዓት የተመዘገበበት ቀን
2. የካሳ ማህደር ቁጥር
3. ያተ/ክልል/000/ዓ.ም በሚል በአጭር የተፃፉ በሚከተለው መንገድ የሚተረጎሙ፡

   ሀ. ያተ ፡- ያልታወቀ ተሽከርካሪ

   ለ. ክልል ፡- አደጋው የደረሰበት ክልል

   ሐ. 000 ፡- የካሳ መዝገብ ላይ የተመዘገበበት ቁጥር

   መ. ዓ.ም ፡- ዓመተ ምህረት/ዘመን

4. የተጎጂው ስም ፣ የአደጋው ቀን ፣ የአደጋው ቦታ
5. አደጋውን ሪፖርት ያደረገው ሰው፣ ድርጅት ወይም ተቋም ስም፣ አድራሻ እና ምርመራ
6. አደጋውን የመረመረው ትራፊክ ፖሊስ ፣ ፖሊስ ወይም መንግስታዊ አካል ስምና አድራሻ
7. የካሳ ክፍያ መጠን
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 መሰረት የሚገለጸው የካሳ መጠን የሚከተሉትን ዝርዝሮች መያዝ አለበት፡-

   ሀ. የተያዘ አጠቃላይ መጠባበቂያ

   ለ. የህክምና አገልግሎት (የተከፈለ፣ቀሪ)

   ሐ. አካል ጉዳት (የተከፈለ ቀሪ)

   መ. ሞት (የተከፈለ ፣ ቀሪ)

   ሠ. ሌሎች ክፍያዎች

   ረ. አጠቃላይ ክፍያ

9. በዚሁ አንቀጽ ንዕስ አንቀጽ 1-8 ከተጠቀሰው የካሳ ጥያቄ የአመዘጋገብ ስርዓት በተጨማሪ አገልግሎቱ ለዚህ ብሎ በአዘጋጀው የዲጂታል ስርዓት መሰረት ይመዘግባል፡፡

## 20. በአደጋ ምርመራ ወቅት ግምት ውስጥ የሚገቡ ሁኔታዎች

1. ባልታወቀ ተሽከርካሪ ወይም የመድን ሽፋን በሌለው ተሽከርካሪ አደጋ የደረሰበት ተጎጂ ፣ ካሳ የመጠየቅ መብት ያለው ሰው ወይም የሕክምና ተቋም የሚመለከተው የትራፊክ ፖሊስ ፣ ፖሊስ ወይም የመንግስት አካል የአደጋውን ምርመራ የተመለከተ ሪፖርት እንዲሰጠው በተመዘገበ ደብዳቤ መጠየቁን ማረጋገጥ
2. የአደጋ ምርመራ ሪፖርት በካሳ ጠያቂው የቀረበ ከሆነ ሪፖርቱን የሰጠው አካል ማረጋገጫ እንዲሰጥ በደብዳቤ መጠየቅ፡፡
3. በጉዳዩ ወይም በአደጋው ውስብስብነት ወይም በሌሎች ምክንያቶች አጠራጣሪ ጉዳዮች ካሉ ፡-

ሀ. የድህረ ትራፊክ አደጋ እና መድን አገልግሎት ዘርፍ ስር ያለ ሠራተኛ በመመደብ የአደጋ ማጣራት ሂደቱን እንዲያከናውን ማድረግ ወይም፣

ለ. የግል የመድን ኩባንያ ሙያተኛ የአደጋውን ሁኔታ እንዲያጣራ መመደብ ይችላል።

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የአደጋን ሁኔታ እንዲያጣራ ለተመደበ አጣሪ የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ እንደ ሁኔታው የመድን ኢንድስትሪውን ልምድና አሰራር ተከትሎ በድርድር ይወሰናል።

## 21. የአደጋ ምርመራ ወይም የማጣራት ተግባር የመፈፀሚያ ጊዜ

የአደጋ ምርመራ ሪፖርትና የማጣራት ተግባሩ እንደ አደጋ ቦታው ርቀት ሊለያይ ቢችልም በልዩ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር ከ10 የሥራ ቀናት በላይ መብለጥ የለበትም፡

## 22. የካሳ ጥያቄው ደጋፊ ሰነዶችን ስለመጠየቅ

1. የድህረ ትራፊክ አደጋ መድን አገልግሎት የሥራ ዘርፍ የካሳ ክፍያ ጥያቄን በተመለከተ ምርመራ እየተካሄደ እያለ ደጋፊ ሰነዶች እንዲቀርቡ አስፈላጊ ሲሆን ለተጎጂው ወይም ለወኪሉ አንድ ወር ወይንም አስፈላጊ ሲሆን ከአንድ ወር በላይ የሚሆን የጊዜ ገደብ በማስቀመጥ ደጋፊ ሰነዶቹ እንዲቀርቡ ይጠይቃል።
2. አገልግሎቱ ለካሳ ጠያቂዎች የላከው የመጀመሪያው ደብዳቤ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መልስ ካላገኘ ሁለተኛ የማሳሰቢያ ደብዳቤ የጊዜ ገደቡ ካለቀ ቀጥሎ ባለው የሥራ ቀን ደጋፊ ሰነዶቹ እንዲቀርቡ የሚጠይቅ ደብዳቤ በድጋሚ ለተጎጂው ወይም ለወኪሉ ይልካል።
3. የሁለተኛ ማሳሰቢያ ደብዳቤ ምላሽ ካላገኘ ደጋፊ ሰነዶችን እንዲያቀርቡ የሚጠይቅ ደብዳቤ ለሶስተኛ ጊዜ ለተጎጂው ወይም ለወኪሉ ይልካል።
4. ለሶስተኛ ጊዜ በተፃፈው ደብዳቤ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ደጋፊ ሰነዶች የማያቀርቡ ከሆነ የካሳ ጠያቂዎቹን በግንባር በማነጋገር የተገኘውን ውጤት በሪፖርት መልክ ከማህደሩ ጋር በማያያዝ ለድህረ ትራፊክ አደጋ ሰአገልግሎት እና መድን አስተዳደር መሪ ሥራ አስፈፃሚና ለአገልግሎቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ የውሳኔ ሃሳብ መቅረብ አለበት።

## 23. ለተጎጂዎችና ለካሳ ጠያቂዎች መልስ መስጠት

1. አደጋው በተገለጸ ወይም የካሳ ጥያቄው በቀረበ በአንድ ቀን ውስጥ ለአገልግሎቱ ጥያቄው እንደደረሰው በማሳወቅ መቅረብ ያለባቸውን ሰነዶች በመዘርዘር በጽሁፍ መልስ መስጠት አለበት፡፡
2. የአደጋ ምርመራ ሪፖርትና ማጣራት ተግባር እንዲሁም የአደጋው ውስብስብነት ወይም ሌሎች አጠራጣሪ ጉዳች ካሉ የካሳ ጥያቄው በቀረበ በአንድ ወር ግዜ ውስጥ አገልግሎቱ በጽሑፍ መልስ መስጠት አለበት፡፡
3. የካሳ ጥያቄው ተቀባይነት ያለው ከሆነ የማጣራቱ ተግባር እንደተከናወነ የካሳ ክፍያው በአምስት የሥራ ቀን እንዲጠናቀቅ በመግለጽ  መልስ መስጠት አለበት፡፡

## 24. የካሳ ክፍያ ጥያቄ ስለማቅረብ

1. ባልታወቀ ወይም መድን በሌለው ተሽከርካሪ የደረሰ የአካል ጉዳትን በተመለከተ የሚቀርብ የካሳ ጥያቄ በቀጥታ በተጎጂው አማካኝነት ወይም በተወካዩ አማካኝነት መቅረብ ይችላል፡፡
2. ባልታወቀ ወይም መድን በሌለው ተሽከርካሪ የደረሰ የሞት አደጋ ካሳ ጥያቄ በሟች መሞት ምክንያት በመተዳደሪያ ረገድ የተቋረጠባቸውን ጥቅም ወራሾች በቀጥታ ወይም በተወካያቸው አማካኝነት ማቅረብ ይችላሉ፡፡

## 25. የጉዳት ዓይነቶች

1. የመድን ዋስትና በሌለው ወይንም ባልታወቀ ተሽከርካሪ የሚደርሱ አደጋዎች የሚከተለው ደረጃ ይኖራቸዋል፡-

   ሀ.ጊዜያዊ የአካል ጉዳት

   ለ.ዘላቂ የሆነ ከፊል የአካል ጉዳት

   ሐ.ዘላቂ የሆነ ሙሉ የአካል ጉዳት

2. ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም «የሞት አደጋ» ማለት ባልታወቀ ወይም መድን ባልተገባለት ተሽከርካሪ የደረሰ የአካል ጉዳት ውጤት የሞት አደጋን ሲያስከትል ነው፡፡

3. ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም «የአካል ጉዳት» ማለት ባልታወቀ ወይም መድን ባልተገባለት ተሽከርካሪ በተጎጂ አካል ላይ የደረሰ ማንኛውም ጉዳት ነው፡፡
4. ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም «ጊዜያዊ የአካል ጉዳት » ማለት ተጎጂው በደረሰበት አደጋ ለተወሰነ ጊዜ በሙሉ ወይም በከፊል የተለመደ ሥራውን ለማከናወን እንዳይችል የሚያደርገው የአካል ጉዳት ነው፡፡
5. ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም «ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት» ማለት ጉዳት የደረሰበት ተጎጂ የተለመደ ሥራውን የመስራት ችሎታው በዘላቂነት የሚቀንስና የማይድን ጉዳት ነው፡፡
6. ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም «ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት» ማለት ጉዳት የደረሰበት ተጎጂ አካሉ ማንኛውም ክፍል ላይ የደረሰበት የማይድን ጉዳት ነው፡፡

## 26. ለአካል ጉዳት እና ለሞት የካሳ ጥያቄ መቅረብ ያለባቸው ደጋፊ ማስረጃዎች

1. ለጊዜያዊ የአካል ጉዳት የሚቀርብ የካሳ ጥያቄ ከሚከተሉት ደጋፊ ሰነዶች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡-

    ሀ. የሕክምና ምስክር ወረቀት

    ለ. ሐኪም መድኃኒት ያዘዘበት ማስረጃ

    ሐ. መድኃኒት የተገዛበትና የሕክምና ወጪ ሕጋዊ ደረሰኝ

    መ. የገቢ መጠን መግለጫ

    ሠ. ማንነቱን የሚገልጽ መታወቂያ

    ረ. የፖሊስ ሪፖርት

    ሰ. ልዩ ልዩ ወጪዎች

2. በዚህ አንቀጽ ንዕስ አንቀጽ 1 (ለ) ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሐኪም መድኃኒት ያዘዘበት ማስረጃ መቅረብ ካልቻለ ለተጎጂው ህክምና የሰጠው ተቋም ወይም ፋርማሲ የህክምና የወጪ ዝርዝር ማስረጃ መስጠት አለበት፡፡

3. ለዘላቂ ከፊል ወይም ሙሉ የአካል ጉዳት የሚቀርብ የካሳ ጥያቄ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተዘረዘሩት በተጨማሪ የሕክምና ቦርድ ማስረጃ ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡
4. ለወደፊት የሚደርሱ የአካል ጉዳቶችን ተጎጂው የሚያረጋግጠው በማስረጃ ሲሆን ተጎጂው የደረሰበትንና ለወደፊት የሚደርስበትን ጉዳት ህጋዊ ማስረጃ በማቅረብ ማረጋገጥ አለበት፡፡
5. ለሞት አደጋ የሚቀርብ የካሳ ጥያቄ ከሚከተሉት ደጋፊ ሰነዶች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡-

    ሀ. የአሟሟቱን ሁኔታ የሚገልጽ የአስክሬን ምርመራ ወይም (outopsy) (ኦቶፕሲ) የሐኪም ማስረጃ

    ለ. የሕጋዊ ወራሾች የፍርድ ቤት ውሳኔ፣

    ሐ. የወራሾች ከሟች ጋር ያላቸው ዝምድና እና የእድሜ ማረጋገጫ ሰነድ፣

    መ. የሟች የገቢ መጠን፣

    ሠ. የሟች የሞት ሰርተፍኬት

    ረ. የሟችና ወራሾች መታወቂያ

    ሰ. የፖሊስ ሪፖርት

## 27. የጉዳት ካሳ አተማመን

በጉዳት ዓይነቶች የካሳ አተማመን ውስጥ የሚከተሉት ጉዳዮች መታየት አለባቸው፡-

1. የአካል ጉዳት የደረሰበት ሰው ግልጽ የሆነ እና የደረሱ ጉዳቶችን የካሳ መጠን ለመወሰን ለህክምና ያወጣው ወጪ፤ የገጠመው የገቢ መቋረጥ፤ተጎጂው ህክምና ሲከታተል የቆየበት ግዜ እና ሌሎች ወጪዎች፡፡
2. ዘላቂ የአካል ጉዳት የደረሰበት ሰው ግልጽ የሆኑ እና ወደፊት የሚደርሱ ጉዳቶች የካሳ መጠን ለመወሰን ተጎጂው የሚያጣው ገቢ ወይም የሚያወጣው ወጪ፤የተጎጂው ዕድሜ፤ ተጎጂው የተለመደ ስራውን የመስራት ችሎታ በዘላቅነት የሚቀንስበትን መጠን (የህክምና ቦርድ ማስረጃ)፡፡

3. ጉዳቱ ሞት ያስከተለ እንደሆነ በሟች ሞት ምክንያት ወራሾች በመተዳደሪያ ረገድ የተቋረጠባቸውን ጥቅም ለማስላት የሟች የገቢ መጠን፤ የሟች እና የወራሾች ዕድሜ፤ወራሾች ከሟች ሲያገኙ የነበረው የገቢ መጠን ፡፡
4. የአካል ጉዳት የደረሰበት ወይም የሟች ወራሾች ግልፅ የሆነ እና ወደፊት የሚያጣውን ገቢ በህጋዊ ማስረጃ ማረጋገጥ ካልተቻለ የካሳ ጉዳቱን ለማስላት ተጎጂው በአምራች ዕድሜ ላይ የሚገኝ ከሆነ ወቅታዊ የአገሪቱን የነፍስ ወከፍ ገቢ መሰረት በማመድረግ የካሳ መጠኑ ይሰላል፡፡
5. ተገቢው ማስረጃዎች ከቀረቡ በኋላ የካሳ ጥያቄው ተቀባይነት ሲገኝ የካሳ ፈጻሚው ከድህረ ትራፊክ አደጋ መድን አገልግሎት ዴስክ ኃላፊ እና ከድህረ ትራፊክ አደጋ አገልግሎትና መድን አስተዳደር መሪ ስራ አስፈፃሚ ጋር በጋራ በመወያየት ያገኘው ውጤት ላይ በመመርኮዝ የጉዳት ካሳ መጠኑን በተመለከተ ያለውን አስተያየትና የውሳኔ ሃሳብ አጭር ሪፖርት በማዘጋጀት እንዲፀድቅለት ለካሳ ክፍያ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡
6. የካሳ ክፍያ ኮሚቴ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 የተተመነውን የጉዳት ካሳ መጠን ካጸደቀው የድህረ ትራፊክ አደጋ መድን አገልግሎት ዴስክ ኃላፊ የጉዳት ካሳ መጠኑን እና የተመኑ መጠን የተሰላበትን መንገድ ለተጎጂዎች በግልጽ ያስረዳል፡፡
7. የድህረ ትራፊክ አደጋ መድን አገልግሎት ዴስክ ኃላፊ በተገቢው መንገድ አስረድቷቸው ተጎጂዎች ካሳ መጠኑ ላይ ከተስማሙ የጉዳት ካሳ ክፍያው እንዲፀድቅ ለሚመለከተው የካሳ አጽዳቂ አካል እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡
8. የድህረ ትራፊክ አደጋ መድን አገልግሎት ዴስክ ኃላፊ በተገቢው መንገድ አስረድቷቸው ተጎጂዎች የካሳ መጠኑ ላይ ካልተስማሙ ቅሬታቸውን ለአገልግሎቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በቃል ወይም በደብዳቤ ማቅረብ ይችላሉ፡፡
9. በአገልግሎቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚው ውሳኔ ከተስማሙ የድህረ ትራፊክ አደጋ መድን አገልግሎት ዴስክ ኃላፊ የጉዳት ካሳ ክፍያው በተስተካከለው መጠን እንዲጸድቅ ለሚመለከተው የካሳ አጽዳቂ አካል እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡
10. በዋና ሥራ አስፈፃሚው ተጨማሪ ክፍያ ከተወሰነላቸው ድህረ ትራፊክ አደጋ መድን አገልግሎት ዴስክ ኃላፊ የጉዳት ካሳ ክፍያው በተስተካከለው መጠን እንዲፀድቅ ለሚመለከተው የካሳ አጽዳቂ አካል እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡

11. በአገልግሎቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ውሳኔ ላይ ተጎጂዎች ካልተስማሙ ቅሬታቸውን ለአገልግሎቱ ቦርድ እንዲያቀርቡ የድህረ ትራፊክ አደጋ መድን አገልግሎት የስራ ዘርፍ ይመራቸዋል፡፡ ዋና ሥራ አስፈፃሚው የወሰነውን ውሳኔ አስመልክቶ ለአገልግሎቱ ቦርድ የሚቀርብ ቅሬታ በ10 የሥራ ቀን ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

12. የአገልግሎቱ ቦርድ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሆናል፡፡

## 28. የካሳ ክፍያ ኮሚቴ

1. በአገልግሎቱ ውስጥ የሚከተሉትን የያዘ የካሳ ክፍያ ኮሚቴ ያዋቅራል፡-

   ሀ. የድህረ ትራፊክ አደጋ አገልግሎት እና መድን አስተዳደር መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቅራቢ እና ሰብሳቢ

   ለ. የስትራቴጂክ ጉዳዮች ስራ አስፈፃሚ አባል

   ሐ. የሕግ አገልግሎት ሥራ አስፈፃሚ አባል

   መ. የድህረ ተራፊክ አደጋ መድን አገልግሎት ዴስክ ኃላፊ አባል እና ፀሐፊ

2. የቀረበው የካሳ ጥያቄ በድህረ ትራፊክ አደጋ መድን አገልግሎት ዴስክ ኃላፊ ተዘጋጅቶና ተፈርሞ ለድህረ ትራፊክ አደጋ አገልግሎትና መድን አስተዳደር መሪ ስራ አስፈፃሚ ይቀርባል፡፡
3. የድህረ ትራፊክ አደጋ አገልግሎትና መድን አስተዳደር መሪ ስራ አስፈፃሚ እና የካሳ ክፍያ ኮሚቴ አጣርተውና ፈርመው ለአገልግሎቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ያቀርባሉ፡፡
4. በአገልግሎቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚው የካሳ ክፍያው ትክክለኛነት ታምኖበት ሲፀድቅ ክፍያው ይፈፀማል፡፡
5. የካሳ ክፍያ ቅጽ ተሞልቶ እና ተፈርሞ ለካሳ ክፍያ ኮሚቴ የሚቀርበው በድህረ ትራፊክ አደጋ አገልግሎት እና መድን አስተዳደር መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቅራቢነት ነው፡፡
6. ካሣ ጥያቄ መጠኑ በአንድ አደጋ (የካሳ ጥያቄ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 በተቀመጠው ሰንጠረዥ ላይ በሀ.3 ከተቀመጠው በላይ የሆኑ ክፍያዎች በአገልግሎቱ የካሣ ክፍያ ኮሚቴ ወይም በሚመለከተው አካል መጽደቅ አለባቸው፡፡

7. ከላይ በንዕስ አንቀጽ 6 ከተጠቀሰው ውጭ ያሉት የካሳ ክፍያዎች ማለትም በዚህ አንቀጽ በተቀመጠው ሰንጠረዥ ላይ ሀ.1 እና ሀ.2 ላይ የተዘረዘሩት የካሳ ክፍያዎች በድህረ ትራፊክ አደጋ መድን አገልግሎት ዴስክ ኃላፊ እና በድህረ ትራፊክ አደጋ አገልግሎት እና መድን አስተዳደር መሪ ሥራ አሥፈፃሚ የሚወሰኑ ይሆናል፡፡

| ተ.ቁ | የካሣ ጥያቄው ዓይነት | ሀ.1.(ብር) | ሀ.2.(ብር) | ሀ.3.(ብር) | ሀ.4.(ብር) |
|---|---|---|---|---|---|
| i | ለአስቸኳይ የሕክምና ወጪ | | | | |
| | በአንድ ሰው ካሳ ጥያቄ | እስከ1000 | | | |
| | በአንድ አደጋ | አስከ3000 | እስከ6000 | እስከ10,000 | ከ10,000 በላይ |
| ii | የሕክምና ወጭ | | | | |
| | በአንድ ሰው | እስከ5000 | እስከ10,000 | እስከ ጣሪያ | |
| | የካሳ ጥያቄ በአንድ አደጋ | አስከ10,000 | እስከ20,000 | እስከ30,000 | ከ30,000በላይ |
| iii | የአካል ጉዳት | | | | |
| | በአንድ ሰው | እስከ10,000 | እስከ20,000 | እስከ ጣሪያ | |
| | የካሳ ጥያቄ በአንድ አደጋ | እስከ20,000 | እስከ50,000 | እስከ 100,000 | ከ100,000በላይ |
| iV | የሞት አደጋ (በአንድ ሰው) | እስከ10,000 | እስከ20,000 | እስከ ጣሪያ | |
| V | ካሣ ጥያቄ በአንድ አደጋ | እስከ20,000 | እስከ50,000 | እስከ 100,000 | ከ100,000 በላይ |

8. በክልል እና በከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ በተደራጁ የድህረ ትራፊክ የስራ ክፍል ሀላፊ የካሳ ክፍያ በተመለከተ በዋና ዳይሬክተሩ አማካኝነት የካሳ ክፍያ ኮሚቴ እንዲዋቀር ይደረጋል፡፡

## 29. የካሣ ክፍያ ስለመፈጸም

1. የድህረ ትራፊክ አደጋ መድን አገልግሎት ዴስክ የካሣ ተከፋዮች ለደረሰባቸው ጉዳት አገልግሎቱ ያለበትን ኃላፊነት በአዋጁ መሰረት የጉዳት ካሣ በመክፈል የተወጣ መሆኑን ለዚሁ በተዘጋጀው የካሳ ክፍያ ስምምነት ላይ በማስፈረም ከማህደሩ ጋር ያያይዛል፡፡
2. በዚህ መመሪያ መሠረት የጸደቁ የካሣ ክፍያ ጥያቄዎች የፈንድ አካውንታት ተገቢውን ማጣራት በማድረግ የካሣ ክፍያ ቼክ እና ቫውቸር በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል አቅርቦ ያስፈርማል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተዘጋጀውን የካሣ ክፍያ ቼክ እና ቫውቸር የተጐጂዎችን መታወቂያ ወረቀት ኮፒ በማያያዝ እና በማስፈረም በአንድ የሥራ ቀን ውስጥ ክፍያ ይፈጽማል፡፡
4. የካሳ ክፍያ የተፈፀመበት የካሳ ማህደር ለድህረ ትራፊክ አደጋ መድን አገልግሎት ዴስክ ያስተላልፋል፡፡
5. የካሳ ክፍያ የተፈፀመላቸው ተጎጂዎች የእርካታ ማረጋገጫ ፎርም እንዲሞሉ ይጠይቃቸዋል፡፡

## 30. አገልግሎቱ የከፈለውን የካሳ ክፍያ ወጪ ማስመለስ

1. ለተጎጂዎች የካሳ ክፍያ የተፈፀመባቸውን የካሳ ማህደር የድህረ ትራፊክ አደጋ መድን አገልግሎት ዴስክ ወጪው ተመላሽ እንዲደረግ ለአገልግሎቱ ለህግ አገልግሎት ስራ አስፈጻሚ ይሰጣል፡፡
2. የአገልግሎቱ ጉዳት ካሳ የከፈለበት መረጃ የሚመዘገብበት የአመዘጋገብ ስርዓት ያዘጋጃል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት የተዘጋጀው የአመዘጋገብ ስርዓት ጉዳት ባደረሱ አካላት ላይ የአገልግሎቱን ወጭ በሕግ ፊት የማስመለስ ተግባር የይርጋ ጊዜው ሳያልፍ ለመጀመርና ለመከታተል ያግዛል፡፡
4. መድን የሌላቸው ተሽከርካሪዎች ባደረሱት ጉዳት ለከፈለው ወይም ለሚከፍለው ካሣ አገልግሎቱ አደጋውን እንዳወቀ ለተሽከርካሪው ባለንብረት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የማስመለስ ተግባሩን መጀመር አለበት፡፡

5. ያልታወቁ ተሽከርካሪዎች ባደረሱት ጉዳት አገልግሎቱ ለከፈለው ካሳ የትራፊክ ፖሊስ ወይም ፖሊስ አጣርቶ የአሽከርካሪውን ወይም የተሽከርካሪውን ባለንብረት አድራሻ ካሳወቀበት ጊዜ ጀምሮ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የማስመለስ ተግባሩን መጀመር አለበት፡፡
6. አገልግሎቱ ያወጣውን ወጭ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 እና 5 በተሰጣቸው ማስጠንቀቂያ ላይ በተገለጸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልፈጸሙ ጉዳት አድራሾች የሕግ አገልግሎት ሥራ አስፈፃሚ ክስ በመመስረት ክትትል ያደርጋል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የመድን ሰጪ ኩባንያዎች የሚፈጸም የካሳ አከፋፈል ዝርዝር ሁኔታ

### 31. የመድን ሰጪ ኩባንያዎች ዝርዝር የካሳ አፈፃፀም ሥርዓት

1. የመድን ኩባንያዎች መድን ለተገባላቸው ተሽከርካሪዎች ለሚፈጽሙት የካሳ አፈጻጸም ስርአትን በተመለከተ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 26 ንዕስ አንቀጽ ከ1 እስከ 5 የተዘረዘሩትን በተጎጂው ወይም በወራሾች መቅረብ ያለባቸውን ደጋፊ ሰነዶች ተያይዞ እንዲቀርብ ማድረግ አለባቸው፡፡
2. የመድን ኩባንያዎች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 27 ንዕስ አንቀጽ ከ1 እስከ 4 የተዘረዘሩትን በጉዳት ዓይነቶች የካሳ አተማመን ውስጥ መታየት ያለባቸውን ጉዳዮች ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው፡፡
3. የመድን ኩባንያዎች መድን ለተገባላቸው ተሽከርካሪዎች ለሚፈጽሙት ካሳ፤ የካሳ አፈጻጸም ስርአትን በተመለከተ ከመድን ኩባንያዎች እና ከኢንዱስትሪው ማህበር ጋር በመመካከር ስምምነት የሚደረስበት ዝርዝር ሁኔታ በጽሁፍ ተዘጋጅቶ ህብረተሰቡ እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡

# ክፍል አምስት

# የሶስተኛ ወገን መድን ሽፋን ሳይኖራቸው በመንገድ ላይ እንዲሽከረከሩ ስለተፈቀደላቸው ተሽከርካሪዎች

## 32. የሦስተኛ ወገን መድን ሽፋን የመግባት ግዴታ የሌለባቸው ተሽከርካሪዎች

1. የመከላከያ ሚኒስቴር የሚጠቀምባቸው ሆነው በሀገር መከላከልና ደህንነት ተግባር በግንባር ቀጠና የተሰማሩ ወይም ከዋና መንገድ ውጭ የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች በዚህ መመሪያ መሰረት የሦስተኛ ወገን የመድን ሽፋን እንዲገቡ አይገደዱም፡፡
2. የመከላከያ ሚኒስቴር የሦስተኛ ወገን መድን ሽፋን ሊኖራቸው የሚገቡ ተሽከርካሪዎችን ዝርዝር እንዲያሳውቅ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጠያቂነት ለመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት ያሳውቃል፡፡
3. የመከላከያ ሚኒስቴር የሶስተኛ ወገን መድን ከመግባት ግዴታ ነጻ የተደረጉ ተሽከርካሪዎች ለሚያደርሱት አደጋ በአዋጁ መሠረት ለተጎጂዎች ካሳ የመክፈል ኃላፊነቱ የተጠበቀ ነው፡፡
4. የሦስተኛ ወገን መድን ሽፋን ሳይገቡ እንዲሽከረከሩ የተፈቀደላቸው ተሽከርካሪዎች የሦስተኛ ወገን የዲጅታል መድን ሽፋን ምስክር ወረቀት እንዲይዙ አይገደዱም፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተገለፀው ቢኖርም የመከላከያ ሚኒስቴር ለተሽከርካሪዎቹ ልዩ ምልክት ወይም ማስረጃ ሊሰጣቸው ይችላል፡፡

## 33. የአከፋፈል ሥርዓት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 32 መሠረት የመከላከያ ሚኒስቴር ተሽከርካሪዎቹ የሦስተኛ ወገን መድን ሽፋን እንዳይገባ የተደረገ ሲሆን ለሚጠቀምባቸው ተሽከርካሪዎች በአዋጁ መሠረት ያለበትን የክፍያ ኃላፊነት መወጣት የሚችልበት አሰራር በተመለከተ ከአገልግሎቱ ጋር የውል ስምምነት ማድረግ አለበት፡፡

## 34. ክፍያ ስለመፈፀም

የሦስተኛ ወገን መድን ሽፋን እንዳይገባ የተደረገው የመከላከያ ሚኒስቴር የሚጠቀምበት ተሽከርካሪ አደጋ ባስከተለ ጊዜ የመድን ሽፋን እንዲገባ ቢደረግ ይከፍል የነበረውን ሶስተኛ ወገን የሀላፊነት መጠን ለአገልግሎቱ ገቢ ያደርጋል፡፡

## ክፍል ስድስት

## የባለድርሻ አካላት ተግባር እና ሀላፊነት

## 35. የአገልግሎቱ ተግባር እና ሀላፊነት

1. አዋጁን እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችን እና መመሪያዎችን ያስፈጽማል፡፡
2. የዲጅታል የሶስተኛ ወገን መድን አስተዳደር ስርዓቱን ተግባራዊነት ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡
3. በአዋጁ አንቀጽ 20 መሰረት በተሽከርካሪ አደጋ ተጎጂዎች የጉዳት ካሳ እንዲከፈላቸው ያደርጋል፡፡
4. በተሽከርካሪ አደጋ ለደረሰ ጉዳት ካሳ የተከፈለባቸው የሞት፣ የአካል ጉዳት እና የንብረት ውድመት መረጃዎችን በመሰብሰብ የአሰራር ክፍተቶችን ለማሻሻል የሚያስችሉ ጥናቶችን ያከናወናል፣ ግንዛቤ ይሰጣል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፡፡

## 36.የመድን ሰጪ ኩባንያዎች ኃላፊነት

1. ማንኛውም የሦስተኛ ወገን መድን ሽፋን የመስጠት ግዴታ ያለበት መድን ሰጪ አገልግሎቱ በዘረጋው የዲጂታል ቴክኖሎጂ የሶስተኛ ወገን መድን ስርዓት መሰረት ለመድን ገቢው ውል የመስጠት ግደታ አለበት ::
2. ማንኛውም መድን ሰጪ በዲጂታል የሶስተኛ ወገን መድን ሽፋን ከሚሰበሰበው የአርቦን ተመን ላይ ተጨማሪ 10% ፈንድ ታሪፍ ገቢ መደረጉን ማረጋገጥ አለበት፡፡
3. የዲጅታል ስርዓቱ ከሚልከው የአድሳት ማስታወሻ መድን ሰጪው ሦስተኛ ወገን ኢንሹራንስ እድሳት ቀን ከማለቁ በፊት ለመድን ገቢው የማስታወሻ መላክ  አለበት፡፡
4. የሶስተኛ ወገን የውል ዘመኑ ካለቀ በኃላ እድሳት ያላደረጉ መድን ገቢዎችን ለአገልግሎቱ ፤ ለትራፊክ ፖሊስና ለክልል የመንገድ ትራንስፖርት ተቆጣጣሪዎች መረጃ ይሰጣል፡፡
5. በአዋጁ እና አዋጁን ለማስፈጸም በወጡ ደንቦንች እና መመሪያዎች መሠረት የካሳ ክፍያ አፈጻጸምን ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

## 37. የፖሊስ ወይም ትራፊክ ፖሊስ ሀላፊነት

1. ማንኛውም የትራፊክ ፖሊስ የተሽከርካሪ አደጋ በደረሰ ጊዜ በተዘጋጅው የመንገድ ትራፊክ አደጋ መረጃ  አስተዳደር ስርዓት ወይም በአገልግሎቱ ወይም በመድን ሰጪው የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት መረጃውን ለሚመለከተው አካል  መላክ አለበት፡፡
2. በተዘረጋው የዲጅታል የሶስተኛ ወገን መድን አስተዳደር ስርዓት መሰረት የሶስተኛ ወገን የመድን ሽፋን እንዲኖራቸው በአስገዳጅነት ለተደነገገባቸው ተሽከርካሪዎች የጸና የመድን ሽፋን ያላቸው ስለመሆን ወይም አለመሆን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡
3. የአዋጁን እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦች እና መመሪያዎችን ድንጋጌ ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም ሰው በህግ አግባብ  እንዲቀጣ ያስደርጋል፡፡
4. በአዋጁ አንቀጽ 13 መሠረት ዲጂታል የመድን ምስክር ወረቀት አለመያዝ እና አለመኖር የመድን ሽፋን እንደሌለው ስለሚያስቆጥረው

ዲጂታል የመድን የምስክር ወረቀት እስኪመጣ ድረስ ፖሊስ ተሽከርካሪውን ይዞ ለማቆት ስልጣን ያለው ሲሆን ይህንን ሁኔታ አገልግሎቱ እንዲያውቅ መደረግ አለበት።

# ክፍል ሰባት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 38. የተሻሩ መመሪያዎች

1. የተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን አዋጅ ቁጥር 559/2000 መሠረት አድርገው የወጡ መመሪያዎች በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።
2. የተሽከርካሪ አደጋ የሶስተኛ ወገን የመድን ውልና የካሳ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 656/2013 በዚህ መመሪያ ተሽሯል።

## 39. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ሁሉ ሚኒስቴሩ ማሻሻል ይችላል።

## 40. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በትራንስፖርት ሎጂስቲክ ሚንስቴር ከተፈረመበት ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ሀምሌ 6/2016

የትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር